**ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን)**

# 19[*] ኢትዮጵያውያን ከሜክሲኮ እስር ቤት ተፈቱ!

## ‹‹አዲሲቷን ኢትዮጵያ›› መመሥረት መጠነሰፊ ለሆነው የኢትዮጵያ ችግር አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው!!

ባለፈው አርብ የካቲት 18፤2003 ዓም በቺፓስ ሜክሲኮ ከሚገኘው የታፓቼላ እስርቤት ለበርካታ ወራት በእስር ሲማቅቁ የነበሩ 19 ኢትዮጵያውያን ተፈትተዋል፡፡ እስካሁን ባለው የዓለምአቀፍ አሠራር መሠረት ስደተኞች ከ90 ቀናት በላይ በእስር መቆየት እንደሌለባቸው ሆኖም ግን ከዚህ ቀነገደብ የሚያልፉ ከሆነ በነጻ መለቀቅ ወይም ወደመጡበት አገር መመለስ እንዳለባቸው የሚናገር በሆንም እነዚህ ወገኖቻችን ግን እስከ አምስት ወራት ድረስ በእስር ቆይተዋል፡፡ ይህ የመፈታታቸው ዜና ለብዙዎቻችን በተለይም ለቤተሰቦቻቸው ከፍተኛ የደስታ ስሜት የፈጠረ ቢሆም በዓለም ዙሪያ ተበታትነው በስደት ለሚኖሩትና በየቀኑ ግፍ እየተቀበሉ ላሉት ኢትዮጵያውያን መፍትሔ ሰላም፣ ነጻነት፣ ፍትሕና እኩልነት የሰፈነባትን ‹‹አዲሲቷን ኢትዮጵያን›› መመሥረት የማያጠያይቅ ጉዳይ እየሆነ መጥቷል፡፡




ወደተነሳንበት ጉዳይ ስንመለስ፤ በሜክሲኮ እስርቤት ለወራት ሲማቅቁ ከነበሩት እስረኞች ቤተሰቦች ዘንድ የጋራ ንቅናቄያችን ዋና ኃላፊ አቶ ኦባንግ ሜቶ የካቲት 2፤2003 ዓም የስልክ ጥሪ ይደርሳቸዋል፡፡ ከዚያም በማከታተል ከተለያዩ የቤተሰብ አባላት ተደጋጋሚ የስልክ ጥሪዎች ቀጠሉ፡፡ የሁሉም መልዕክት ‹‹ቤተሰቦቻችን አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ ውስጥ እየማቀቁ ነውና እባካችሁን ድረሱላቸው›› የሚል ነበር፡፡ ችግሩ አስከፊ እንዲሆን ካደረጉት

[*] የአጠቃላይ እስረኞቹ ቁጥር 21 ሲሆን የተፈቱት 19 ቢሆኑም የቀሩት ሁለቱ አንዳንድ ሰነዶች ሲሟሉ በጥቂት ቀናት ውስጥ እንደሚፈቱ ባለሥልጣናቱ ቃል ገብተዋል፡፡

ነገሮች መካከል አንዳንዶቹ ሴቶች መሆናቸው እንዲሁም የተወሰኑት የስኳርና የሌሎች አጣዳፊ ዕርዳታ የሚያስፈልጋቸው በሽታዎች ተጠቂ መሆናቸው ነበር፡፡

ታሳሪዎቹ ከአገራቸው እንዲወጡ ያስገደዳቸው በኢትዮጵያ ያለው የሰብዓዊ መብት ረገጣና አፈና እንደሆነ የሚገልጹ ሲሆን የተወሰኑት ተማሪዎች፤ ሌሎቹም የዩኒቨርሲቲ መምህራን፣ የመንግሥት ሠራተኞች፣ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ደጋፊዎች፣ ወዘተ ናቸው፡፡ ሜክሲኮ ሲደርሱ ለእስር ተዳረጉ እንጂ እዚያ ከመድረሳቸው በፊት ያሳለፉት ጉዞ መከራና ሰቆቃ የበዛበት እንደነበር ታሪካቸው ይመሰክራል፡፡ በመጀመሪያ ከተለያዩ የመካከለኛው ምስራቅ አገሮች ወደ ፓናማ በአውሮፕላን ተሳፍረው ይመጣሉ፡፡ ከዚያም ወደ ኮስታ ሪካ ቀጥሎም ኒካራጉዋ፣ ሆንዱራስ፣ ኤልሳልቫዶር እና ጓቴማላን አልፈው ነው ወደ ሜክሲኮ የሚዘልቁት፡፡ ወደዚያ የሚሄዱት አብዛኛዎቹ ኢትዮጵያውያን፣ ኤርትራዊያን እና ሶማሌዎች ሲሆኑ ባለው የተለመደ አሠራር መሠረት ጥቂት ቀናት እስርቤት ከቆዩ በኋላ ከእስር ይለቀቁና ወደ አሜሪካ ለመግባት ጉዳያቸውን መከታተል ይጀምራሉ፡፡ ሆኖም ግን የሌሎቹ አገር ስደተኞች ባጭር ቀናት ውስጥ ሲለቀቁ ኢትዮጵያውያን ግን እስከ አምስት ወራት ድረስ በግፍ ታስረው ሲማቅቁ ቆይተዋል፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው ከታሳሪዎቹ ቤተሰቦች ለጋራ ንቅናቄያችን የሚደርሱ የስልክ ጥሪዎች እየጨመሩ እንዲያውም የአንደኛዋ እስረኛ እህት ለአቶ ኦባንግ ደውላ እህቷ ያለችበትን ሁኔታ ከገለጸች በኋላ አስቸኳይ የሕክምና እርዳታ ካላገኘች በሕይወት የመኖሯ ጉዳይ አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱ እጅግ ሃዘን በተቀላለቀለበት ሁኔታ ከገለጸች ከሁለት ቀናት በኋላ አቶ ኦባንግ ወደሜክሲኮ ጉዟቸውን አቀኑ፡፡ በቀጣይ ቀናትም በሜክሲኮ ከሚገኙ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ጋር በሚነጋገሩበት ወቅት የታሳሪዎቹን ስም እንዲያስረክቡ በተነገራቸው መሠረት አቶ ኦባንግ ቤተሰቦቻቸውን አስፈቅደው የ21ንም ስም ለባለሥልጣናቱ አስረከቡ፡፡

ይህንን ካደረጉ በኋላ አቶ ኦባንግ የተገነዘቡት ዋንኛ ነገር የሌሎች የምስራቅ አፍሪካ አገራት ዜጎች ጉዳያቸው በወቅቱ ታይቶ ሲስተናገዱ ኢትዮጵያውያኑ ግን ይህንን ዓይነት ዕድል አለማግኘታቸውን በመታዘባቸው ጉዳዩን ለሚመለከታቸው የሜክሲኮ ባለሥልጣናት ይገልጻሉ፡፡ በምላሹ ያገኙት ነገር ቢኖር የሌሎቹ አገራት ኤምባሲዎች ለስደተኛ ዜጎቻቸው ፈጣን ምላሽ ሲሰጡ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ግን ምላሽ አለመስጠት ብቻ ሳይሆን **‹‹በወቅቱ በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ ሰላምና መረጋጋት የሰፈነበት ስለሆነ ስደተኞቹ ወደአገራቸው ሊመለሱ ይገባቸዋል››** በማለት የሚከራከር በመሆኑ ለአቶ ኦባንግ ይገልጹላቸዋል፡፡ እንዲያውም ከጥቂት ወራት በፊት ጠ/ሚኒስትራችሁ ሜክሲኮን በጎበኙበት ወቅት በእስር ስላሉ ኢትዮጵያውያን ተጠይቆ የሰጠው ምላሽ **‹‹ሜክሲኮ በዚህ ጉዳይ ላይ የመሰላትን ማድረግ ትችላለች፡፡ ሆኖም ግን እነዚህ ስደተኞች ወደኢትዮጵያ ቢመለሱ ምንም ዓይነት ችግር እንደማይገጥማቸው›› እንዲያውም ‹‹ኢትዮጵያ ባሁኑ ጊዜ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት እያሳየች በመሆኗ መመለሳቸው የሚጠቅማቸው›› መሆኑን ለእነርሱ ጥገኝነት መስጠት አስፈላጊ እንዳልሆነ በመናገሩ ይህ ሁሉ ሁኔታ ሊከሰት መቻሉን ባለሥልጣናቱ በግልጽ ተናግረዋል፡፡** በዚህ ጉዳይ ላይ አቶ ኦባንግ የወቅቱ የኢትዮጵያን ሁኔታ አስመልክቶ ለባሥልጣናቱ ሰፋ ያለና በማስረጃ የተደገፈ ገለጻ አቅርበዋል፡፡

ይህ በሚሆንበት ጊዜና አቶ ኦባንግ በእስር ቤቱ አካባቢ ሳሉ አንድ ኤርትራዊ እጁን ሊሰጥ ወደ እስርቤቱ ሲመጣ እንዲሁም ሌሎች ሁለት ኢትዮጵያውያን ይመለከታሉ፡፡ ሁሉም የራሳቸው የሆነ ታሪክ አላቸው፡- ከመካከላቸው አንዱ ሲናገርም ከኢትዮጵያ ወደ ጅቡቲ ከዚያም ወደ የመንና ዱባይ እንደሄና እዚያው ዱባይ ለሦስት ዓመት ሲሰራ እንደቆየና ባጠራቀመው ገንዘብ ወደ ፓናማ እንደመጣ ከዚያም በጀልባና በእግር ለሦስት ወራት ተጉዞ ሜክሲኮ እንደደረሰ ይተርካል፡፡ በዚህ ጉዞው ውስጥ እጅግ አስፈሪ ጫካዎችንና በረሃዎችን

እንዳቋረጠ፤ ያለምግብ ለቀናት እንደቆየ፤ በየቁጥቋጦው ሲተኛ እንደከረመ፤ ወዘተ እጅግ በሚያሳዝን ሁኔታ ሲተርክ ለሰማው ‹‹የኢትዮጵያውያን መከራ የሚያበቃው መቼ ነው?›› የሚል ጥያቄ እንዲያቀርብ ያስገድዳል፡፡

ሌላኛው ግለሰብ ደግሞ የ21ዓመት ወጣት ሲሆን እጁን ለሜክሲኮ ከሰጠ በኋላ ለ6ወራት የሚቆይበትን ወረቀቱን እንዳገኘ ወደ አሜሪካ ጉዞውን እንደሚያቀና እየተናገረ ሳለ አንዱ በኦሮምኛ ሲያናግረው በመስማታቸው አቶ ኦባንግ ያንን ኦሮምኛ ተናጋሪውን ጠጋ ብለው ሲያነጋግሩት የሰጠው ምላሽ በጣም ልብ የሚነካ ነበር፡፡ እንዲህ ነበር ያለው፡- ‹‹ህወሃት ሥልጣን ሲይዝ የ1 ወይም የ2 ዓመት ህጻን ነበርኩ፡፡ ካደኩ በኋላ ራሴን ለማሻሻል ብዙ ጣርኩ፤ ደከምኩ፡፡ ሆኖም ግን ችግሩ እየባሰብኝ ከመሔድ ሌላ ምንም መፍትሔ ላገኝ አልቻልኩም፡፡ ባሁኑ ጊዜ አዲስ አበባ ብትሄድ ጎዳና ተዳዳሪውና ለማኙ ከተማዋን አጣብቧት ብቻ ነው የምታየው፡፡ በ1997 ምርጫ ለውጥ ይመጣል ብለን ብዙ ተስፋ አድርገን ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ግን የነበረችንም ጭልጭል የምትለው ተስፋችን ተሟጥጣ ጠፋች፡፡ ከዚያ በኋላ በኢትዮጵያ ውስጥ መቆየት ከመሞት ሌላ የሚመጣብን ነገር እንደሌለ ስናውቅ የመሞት የመሞት ለምን ወደውጪ ወጥተን አንሞትም ብለን አገራችንን ጥለን ወጣን፡፡ ብዙ ችግር በኢትዮጵያ አለ፤ በተለይም ደግሞ የዘር ፖለቲካ አገራችንን በጥብጧታል፤ ለዚህ መፍትሔ ካላገኘን የወደፊት ዕጣትችን ምን እንደሚሆን መገመት አያቅትም፡፡›› ይህ በእውነቱ ለሁላችንም ከፍተኛ ትምህርት የሚሰጥ አነጋገር ነው፡፡ ሁላችንም ይህን በጥልቀት ልባስብበትና በአፋጣን ምላሹን ልንሰጥ ይገባናል፡፡ ‹‹ከዘር ይልቅ ለሰብዓዊነት ቅድሚያ የሚሰጥባትን አዲሲቷን ኢትዮጵያን›› ለመመሥረት በቅንነት መትጋት ይገባናል፡፡

የዚህ ወጣት ታሪክ ብቻ ሳይሆን በዚሁ የስደተኛ ማጎሪያ አካባቢ የሚሰማው አሰቃቂ ታሪክ የሰውን ልጅ ነጻነቱን ሲያጣ መከራን ለመቀበል የሚከፍለው መስዋዕትነት ምን ያህል መራራ እንደሚሆን የሚያስረዳ ነበር፡፡ አንዲት ሴት እና ሌሎች ሦስት ኢትዮጵያውያን ያሳለፉትን ሰቆቃ ሲናገሩ ላዳመጠ ‹‹እስከ መቼ›› ብሎ ከመጠየቅ በላይ እንደሚሄድ እሙን ነው፡፡ ወደሚክሲኮ በሚደረገው ጉዞ ሦስት ኢትዮጵያውያን ልጃገረዶች ከደቡብ አሜሪካ ወደ ሰሜን ሲጓዙ መንገድ ስተው ለ17 ቀናት ጥቅጥቅ ባለ ደን ውስጥ ሲባዝኑ ከከረሙ በኋላ ምግባቸው አልቆ በረሃብ ጠውልገውና ኃይል አጥተው በመጨረሻ ዋናውን መንገድ ቢያገኙም ከመንገዱ በኋላ ግን በጎርፍ የሞላ ወንዝ መሻገር የግድ መሆኑን እነዚህ ሦስት ልጃገረዶች ቢገነዘቡም አማራጭ ስላልነበራቸው ወንዙን ለመሻገር ሲሞክሩ ሞገደኛውን ወንዝ ማለፍ አቅቷቸው በጎርፍ ተወስደው በመጨረሻ ላይ የአካባቢው ነዋሪዎች የሁለቱን ሬሳ ያገኙ ሲሆን የአንዲቷ ግን አለመገኘቱን በእንባ ፊቱ እየታጠበ አንደኛው ወጣት ሲተርክ ለተመለከተው ‹‹የዚህ ግፍ ማብቂያ መቼ ነው?›› ብሎ ከመጠየቅ ያለፈ ነገር ለመሥራት እንደሚገፋፋ ጥርጥር የለም፡፡



በእነዚህ ጊዜያት ሁሉ አቶ ኦባንግ ከሜክሲኮ ባለሥልጣናት እንዲሁም ከተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊዎች ጋር የእስረኞቹን መፈታት በተመለከተ ወቅታዊውን የኢትዮጵያ ሁኔታ በማስረዳት ሲነጋገሩ ከቆዩ በኋላ በቀጣዩ ቀን ከባለሥልጣናቱ መካከል የእስረኞቹን መፈታት በማብሰር ለአቶ ኦባንግ የስልክ መልዕክት

ይልካል፡፡ ይህ መልዕክት በእስረኞቹ ቤተሰቦች ዘንድ የፈጠረው እፎይታና የመንፈስ እርካታ ይህ ነው ሊባል የማይችል ሲሆን በሌሎች የዓለማችን ክፍሎች ያሉትን ወገኖቻችንን ስናስበ ደግሞ ደስታችን ቀቢፅ ይሆናል፡፡

የኢትዮጵያውያን መከራ በዚህ ብቻ ተነግሮ የሚያልቅ አይደለም፡፡ አሁን በቅርቡ እንኳን በሊቢያ እንዲሁም በኖርዌይ ያሉ ወገኖቻችን እየረደሰባቸው ያለው መከራ የመገናኛ ብዙሐኑን ገጽ ያጣበበ ነው፡፡ የጋራ ንቅናቄያችንም ከዚሁ ጋር በማያያዝ እነዚህ ወገኖች የሚረዱበትን መንገድ ለመቀየስ ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረገ ሲሆን በተለይ በኖርዌይ ለሚገኙት ችግር መፍትሔ ይረዳ ዘንድ ከአገሪቱ ባለሥልጣናት ጋር ለመነጋገር አቶ ኦባንግ ወደዚያው አምርተዋል፡፡

ይህንን ሁሉ ሲሆን በአገር ውስጥ ያለው ችግር ደግሞ ከቁጥጥር በላይ እየሆነ ከመምጣት አልፎ ግን ጊዜውን ጠብቆ ለመፈንዳት የተዘጋጀ ቦምብ ሆኖ ይታያል፡፡ የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ ዋና ዓላማ ለኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላምን እና ዕድገትን ለማምጣት ሳይሆን በዚያ ሰበብ ከውጪ በዕርዳታ በሚያገኘው ገንዘብ የአገራችንን ሕዝብ አንገት ለማስደፋትና አፉን ለመሸበብ ብሎም በውስጡ ፍርሃት ለመፍጠር ሲጠቀምበት መቆየቱ የሚዘነጋ አይደለም፡፡ ይህንን እውነታ እያወቅን እኛስ ለምንድነው እስካሁን ፍርሃታችንን ፈርተንና ሌሎችን አስፈራርተን ዝም ያልነው? ለችግራችን መንስዔ ዋነኛ ለሆነው ምላሽ እስካልሰጠን ድረስ አሁንም ኢትዮጵያውያን ከአገራቸው ይሰደዳሉ፤ አሁንም ይታሰራሉ፤ አሁንም ይሞታሉ፤ . . . ለዚህ የማያቋርጥ ዑደት ማቆሚያ ማድረግ የምንችለው እኛው መሆናችንን ተገንዝበን ሰላም፣ ዕርቅ፣ እኩልነት፣ ፍትሕ እና አንድነት የሰፈነባትንና ‹‹ከዘር ይልቅ ለሰብዓዊነት›› ቅድሚያ የሚሰጥባትን ‹‹አዲሲቷን ኢትዮጵያ›› ለመመሥረት ፍርሃታችንን ድልነስተን በአንድነት እንነሳ!!

ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን)
*****************************************************************************************************************

*ለዚህ ደብዳቤ ምላሽም ሆነ ለተጨማሪ መረጃ ዋና ዳይሬክተሩን ለአቶ ኦባንግ ሜቶ (obang@solidaritymovement.org) በመጻፍ ወይም በስልክ (202) 725 -1616 በመደወል ወይም ድረገጻችንን (www.solidaritymovement.org) በመጎብኘት ለመረዳት ይችላሉ፡፡*

